
ሁሉን
ለእግዚአብሔር
ክብር
ትምህርት 5 ለሐምሌ 25፣ 2018


(1 ቆሮንቶስ 10:31)
"እንግዲህ የምትበሉ
ወይም የምትጠጡ
ብትሆኑ ወይም ማናቸውን
ነገር ብታደርጉ ሁሉን
ለእግዚአብሔር ክብር
አድርጉት።"

ጳውሎስ ከ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7 ጀምሮ የቆሮንቶስ ሰዎች በደብዳቤ የላኩለትን ጥያቄዎች መመለስ ላይ ትኩረቱን ያደርጋል (1 ቆሮ 7:1)።

ጳውሎስ ከምዕራፍ 8 እስከ 10 ድረስ ዋናው ርዕሱ ጣዖትን የማምለክ ኃጥያትን የተመለከተ ቢሆንም ከዚህ ርዕስ ጋር በቀጥታ የማይገናኙ ልዩ ልዩ ጉዳዮችንም እያነባበረ ይጠቅሳል።

ቢሆንም ግን በእያንዳንዱ ጉዳይ ውስጥ ቤተክርስቲያንን ወደ አንድነት ሊያመሯት የሚችሉ እንደ ፍቅርና መከባበር ያሉ ዋና ርዕሶችን በማስተሳሰር ለማንሳት ሞክሯል።

በጥቅሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ ወይም በግል ህይወት የሚደረግ ማንኛውም ተግባር ለእግዚአብሔር ክብር ሊደረግ እንደሚገባ ጳውሎስ በአንክሮ ያሳስባል።



**1 ቆሮንቶስ 8**

ለጣዖት የተሰዋ ምግብ

(እውቀት እና ፍቅር)

**1 ቆሮንቶስ 9**

ጳውሎስ መብቶቹን መተዉ

(የወንጌል መብቶች)

**1 ቆሮንቶስ 10:1-13**

ስለ ጣዖት አምልኮ ማስጠንቀቂያ

(ከኋላ ታሪክ መማር)

**1 ቆሮንቶስ 10:14-22**

የጌታ ጽዋ እና የአጋንንት ጽዋ

(ከጣዖት መሸሽ)


**1 ቆሮንቶስ 10:23-33**

ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት

(የተፈቀደው እና ተገቢ የሆነው)



# እውቀት እና ፍቅር



## 1 ቆሮንቶስ 8 (ለጣዖት የተሰዋ ምግብ)

"[...] እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል።" (1 ቆሮንቶስ 8:1)

ጳውሎስ የቤተክርስቲያን ሰዎችን "ብርቱ" እና "ደካማ" በማለት ለሁለት ይከፍላቸዋል።

| | | |
|---|---|---|
| 1 ቆሮንቶስ 8:4-7 | ብርቱ የተባሉት ሰዎች ጣዖታት ከንቱ እንደሆኑና አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ይረዳሉ | ደካማ የተባሉት ሰዎች ይህንን ገና በቅጡ አልተረዱትም |
| 1 ቆሮንቶስ 8:7 | ብርቱ የተባሉት ለጣዖት የተሰዋውን ሥጋ ይበላሉ ምክንያቱም ጣዖት ምግባቸውን ሊበክል እንደማችል ያውቃሉ | ደከማ የተባሉት ግን ያንን ሥጋ ከበሉ ኃጥያት እንደሰሩ ያስባሉ |



ነገር ግን ብርቱዎቹ በእውቀታቸውና በተግባራቸው ደካማ የሆኑትን ሊያሰናክሉ ይችላሉ (1 ቆሮ 8:10)። ለወንድሙ ካለው ፍቅር የተነሳ ብርቱ የሆነው ደካማ ለሆነው ሲል ራሱን ሊቆጥብ ይገባል (1 ቆሮ 8:11-13)።

ክርስትያኖች ፍቅርን ከእውቀት በፊት በማስቀደም "ደካማ" ለተባሉት ወንድሞች እውቀት እንቅፋት እንዳይሆንባቸውና እድገታቸውን እንዳይገታው መጠንቀቅ አለባቸው።



# የወንጌል መብቶች

## 1 ቆሮንቶስ 9 (ጳውሎስ መብቶቹን መተዉ)

"እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል።"
(1 ቆሮንቶስ 9:14)

ጳውሎስ ለደካሞች ካለው ፍቅር በመነሳት ቢያንስ ሶስት መብቶችን ትቷል:



* በጉባኤው የመቀለብ መብት (1 ቆሮ 9:4)
  - ጳውሎስ ሌሎች ሐዋርያት ከሚያገለግሏቸው ቤተክርስቲያናት የሚቀበሉትን ድጋፍ እርሱ ከሚያገለግላቸው ቤተክርስቲያናት አልተቀበለም።



* ከሚስቱ ጋር የመጓዝ መብት (1ቆሮ 9:5)
  - ይንከባከቧቸውና በአገልግሎታቸው ይረዷቸው ዘንድ ከሚስቶቻቸው ጋር መጓዝ የሐዋርያት ልማድ ነበረ። ሚስቲቱም እንደባልዋ የቤተክርስቲያንን እርዳታ የመቀበል መብት አላት።



* ተራ ስራን ያለመስራት መብት (1ቆሮ 9:6)
  - ጳውሎስ ከአድማጮቹ ያልተገባ ጥቅምን ለማግኘት እንደሚፈልግ እንዳያስቡና ራስን የመካድ ምሳሌነትን ሊያሳያቸው ሲል ኑሮውን በራሱ ለመቻል ጥሯል።


ኢየሱስ ወንጌልን የሚሰብኩ ሰዎች በወንጌል ስራ እንዲተዳደሩ በግልጽ ቢናገርም፣ ጳውሎስና በርናባስ ግን አማኞችን ላለማደናቀፍ ብለው በፈቃዳቸው ይህንን መብት ትተው ነበር (1ቆሮ 9:12-14፤ ሉቃ 10:7)።




# ከኋላ ታሪክ መማር

## 1 ቆሮንቶስ 10:1-13 (ስለ ጣዖት አምልኮ ማስጠንቀቂያ)

“ሕዝብም ሊበሉ ሊጠጡም ተቀመጡ ሊዘፍኑም ተነሡ ተብሎ እንደ ተጻፈ ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ አትሁኑ።” (1 ቆሮንቶስ 10:7)






የዘጸአት ታሪክ በመንፈሳዊ መነጽር ሲታይ የእኛን ሕይወት ይመስላል። ባህሩን የእስራኤል ሕዝብ መሻገሩ የእኛን የጥምቀት ኪዳን ተምሳሌት ነው (1ቆሮ 10:1-2)።

በምድረ በዳ የበሉት ምግብና መጠጥ የእኛን የጌታ እራት የሚወክል ነው፤ እርሱም በመንፈስ የኢየሱስን ሥጋ እና ደም የምንበላበትና የምንጠጣበት ነው (1ቆሮ 10:3-4)።







ልብ እንበል! ምንም እንኳን እስራኤላውያን እነዚህን ነገሮች ቢፈጽሙም ወደ ጣዖት አምልኮና ሌሎች ከባድ ኃጥያቶች ውስጥ ወድቀው ነበር። ይኸው ተመሳሳይ ነገር እንዳይገጥመን እንጠንቀቅ! (1 ቆሮ 10:5-10)።

ስለዚህም ሐዋርያው ይህንን ክፍል በኃይለኛ ምክር እንዲህ ሲል ይጠቀልለዋል “ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።” (1ቆሮ 10:12)።

# ከጣዖት መሸሽ

## 1 ቆሮንቶስ 10:14-22 (የጌታ ጽዋ እና የአጋንንት ጽዋ)

“ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ጣዖትን ከማምለክ ሽሹ።” (1 ቆሮንቶስ 10:14)



ለጣዖታት የተሰዋን ምግብ ያለ ሀሳብ መብላት ከተፈቀደ ታዲያ ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 10:20 ላይ ይህን ሀሳብ የሚቃወም ምክር እየሰጠ የሚመስለው ለምንድን ነው?

ያለ ማንም ትዝብት ይህን ሥጋ በቤት መብላትና ጣዖታትን ለማምለክ በዓል እያከበረ ባለ ሕዝብ መሃል መብላት ፍጹም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንድ አማኝ በእንዲህ አይነቱ በዓል ላይ ከተሳተፈ እምነቱን ክዶ የጣዖት አምልኮን እየተቀበለ ነው።

በጌታ እራት ላይ ስንሳተፍ የክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያን) እንደምንሆነው በጣዖት በዓላት ላይ ስንሳተፍ ደግሞ ከአጋንንት ጋር እንተባበራለን (1ቆሮ 10:16-20)።



የጌታን እራት ጽዋ እየወሰድንና ኢየሱስን እያመሰገንን በተመሳሳይ ሰዓት ደግሞ ከአጋንንት በዓል ጽዋ መውሰድ አንችልም (1ቆሮ 10:21)።

# የተፈቀደው እና ተገቢ የሆነው

## 1 ቆሮንቶስ 10:23-33 (ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት)

"እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።" (1 ቆሮንቶስ 10:31)

"ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም አይደለም፤" (1 ቆሮ 10:23)።

ሁለት ተጨባጭ ምሳሌዎች:



ለጣዖት የተሰዋ ምግብንና ንጹህ ምግብን ሁለቱንም የሚያቀርብ ሥጋ ቤት ነበር እንበል። ከዚህ ቤት ለመግዛት አንድ አማኝ ቢመጣ ንጹህ ያልሆነውን ሥጋ እንደማይበላው ላለማሳወቅ ሥጋው ከየት እንደመጣ ላይጠይቅ ይችላል።(1ቆሮ 10:25)

አንድ የማያምን ሰው አማኙን ሰው ምግብ ጋበዘው እንበል። አማኙ ያለ ጥያቄ በላ (ሁሉ ነገር ለእርሱ ተፈቅዶአልና)። ደግሞም ጋባዡ የቀረበው ሥጋ ለጣዖት መሰዋቱን ተናገረ እንበል። ይሄን ጊዜ የጋባዡን አመለካከት ላለመማበላሸት ሲል አማኙ ሥጋውን መብላት የለበትም (1 ቆሮ 10:27-29)







ከእነዚህ መመሪያዎች በስተጀርባ ያሉት ሁለት መርሆዎች እግዚአብሔርን በሁሉ ነበር ማክበር(1ቆሮ 10:31) እና ሌሎች እንዲጠቀሙ መፈለግ ናቸው (1ቆሮ 10:24, 32)።

ይህም ማለት ኢየሱስ ያን ባለጸጋ ወጣት እንደጠየቀው እግዚአብሔርን ከሁሉ በላይ መውደድና ባልንጀሮቻችንን እንደ ራሳችን መውደድ ማለት ነው ።

“ሐዋርያው የቆሮንቶስ ሰዎችን " ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ። " ብሎ አስጠነቀቃቸው። በጸሎት መትጋትን ችላ ብለው ትምክህተኛና ትዕቢተኛ ቢሆኑ ወደ ትልቅ ኃጥያት ይወድቃሉ፤ በራሳቸውም ላይ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያመጣሉ። [...]

ጳውሎስ በጌታ ወንድሞቹ የሆኑትን ቃላቸውና ተግባራቸው በሌሎች ላይ የሚፈጥረውን ተጽዕኖ ልብ እንዲሉ ያሳስባቸዋል እናም ማንኛውም ተግባር ምንም እንኳን መልካም ቢመስል ጣዖት ማምለክን የሚያደፋፍር ወይም በእምነት የደከሙትን የሚያሰናክል ከሆነ እንዳያደርጉት ያስጠነቅቃቸዋል። " እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት። … ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ።"

EGW (The Acts of the Apostles, p. 316)